# ነገ ለሚያበቃ

ልምጭ ቆርጦ አይቀጣም ፣ እግዚአብሄር ሲቆጣ
አርቆ እማያስብ ፣ ሀሊናውን ያጣ
በዘር የሰከረ ፣ ስልጣን ላይ ሲያወጣ
ማዘን የዛኔ ነው ፣ ችግር መአት መጣ
ባገር ቀን ጎደለ ፣ ፈጣሪ ተቆጣ ።

ዘመን ተለዋውጦ ፣ ውርጋጥ ከነገሰ
ዝሙት አመንዝራው ፣ ገብቶ ከቀደሰ
ሃይማኖት ተንቆ ፣ ስራት ከረከሰ
የሰው ስብዕናው ፣ ከንስሳት ካነሰ
በፍርደ ገምድሎች ፣ ደም እየፈሰሰ
አገር ነቀዝ በላው ፣ ስሩ በሰበሰ
መፍትሄ አይገኝም ፣ አዝኖ ባለቀሰ
ህዝብ ህሊና ገዝቶ፣ እስካልተመለሰ
ባንድነት ተባብሮ ፣ ካልተንቀሳቀሰ ።

የአዕምሮ ድህነት ፣ ባናቱ ተተክሎ
ከሃዲ ሹምባሹ ፣ ባንዳው ተኮልኩሎ
እንደ ጶሮ ብልት ፣ አገር ተገንጥሎ
ገበሬው ከርስቱ ፣ ከጉልቱ ተነቅሎ
አገር ተሸንሽኖ ፣ ለባዕድ ታድሎ
ሰው በገዛ አገሩ ፣ ታድኖ ተገሎ
ኑሮ እንዴት ይገፋል ፣ ሁሌ ተበድሎ
ያውም በጭንጋፎች ፣ በወያኔ ቆስሎ ።

እንዳበደ ውሻ ፣ የሚቅነዘነዙ
በዘር በጥላቻ ፣ አብደው የነፈዙ
ጥጋብ የነፋቸው ፣ ልክ አጥተው የጦዙ
ስካሩ ካልበቃ ፣ ልቦና ካልገዙ
ግፋቸው ለትውልድ ፣ እንዳይተርፍ መዘዙ ።

ጥጋብ ልክ ይኑረው ፣ ከበሮ ድለቃ
ነገ አንገት ለመድፋት ፣ አያሻም ቡረቃ
ያልባኒያ ካድሬ ፣ ካለልክ ሲነቃ
አገር መበታተን ፣ ወገን ላይ ሽመቃ
ተዋርዶ ማዋረድ ፣ መልከስከሱ ይብቃ
ህዝብን ላትገዙት ፣ ዘወትር በአመቃ
ህሊና ይስጣችሁ ፣ ነገ ለሚያበቃ ።

ታዛቢው … November 01, 2010